# ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፣ ኤም.ዲ.
# የኮቪድ የኪራይ እፎይታ ፕሮግራም የሰነድ ማረጋገጫ ዝርዝር

በሚያመለክቱበት ጊዜ የሚከተሉት ሰነዶች ለመጫን ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጡ ።

## ☐ የፎቶ መታወቂያ

- **የመንጃ ፈቃድ ቅጅ ወይም**
- **የስቴት መታወቂያ ካርድ ቅጅ ወይም**
- **የፓስፖርት ቅጅ ወይም**
- **ለእያንዳንዱ አዋቂ የቤተሰብ አባል ሌላ ኦፊሴላዊ መታወቂያ**

## ☐ የአድራሻ ማረጋገጫ

ለእርዳታ በሚያመለክቱበት አድራሻ የሚኖሩበትን ሰነድ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ ። ይህንን በባንክ መግለጫ (እስቴትመንት) ፣ በህጋዊ ደብዳቤ ፣ በፍጆታ ሂሳብ ወይም አድራሻዎን በሚያረጋግጡ ሌሎች ሰነዶች ማድረግ ይችላሉ።

## ☐ የገቢ ማረጋገጫ

በፕሮግራም ገደብ ውስጥ አጠቃላይ የቤተሰብ ገቢ እንዳለዎት በሰነድ ወይም በራስ ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅብዎታል። ከ 2020 የግብር ተመላሽዎ ወይም ካለፉት 30 ቀናት ሰነዶች ያቅርቡ ። ይህ ሊያካትት የሚችለው፡

- **የክፍያ ወረቀቶች**
- **የወለድ መግለጫዎች**
- **የሥራ አጥነት ካሳ መግለጫዎች**
- **ለ 2020 የቀን መቁጠሪያ ዓመት የአይ.አር.ኤስ(IRS) ቅጽ 1040 ተሞልቷል ፣ ወይም**
- **ከኮቪድ በፊት እና የወቅቱን ገቢ በግልፅ የሚገልጽ የራስ-ማረጋገጫ / የጽሑፍ መግለጫ**

## ☐ የኪራይ መረጃ

የኪራይ ሃላፊነትዎን ፣ የክፍያ ታሪክዎን እና ዕዳዎን ለማሳየት ሰነዶች ማቅረብ ያስፈልግዎታል። ይህ በኪራይ ሂሳብ ፣ በኪራይ ውል ወይም በሌላ ሰነድ ተጣምሮ የሚያስፈልገውን መረጃ በሚያቀርብ ሰነድ ሊሆን ይችላል ።

## አሁኑኑ ያመልክቱ :

## www.mc311.com/rentrelief